## ስለ FARREP

የቤተሰብ እና የስነ ተዋልዶ መብቶች ትምህርት መርሃ ግብር (FARREP) የሴት ልጅ ግርዛት (FGC) በሚፈጸምባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ለባህል ተስማሚ ድጋፍ፣ ትምህርት እና የጥብቅና አገልግሎት ይሰጣል።

በቪክቶሪያ ዙሪያ ካሉ ሴቶች፣ ቤተሰቦች እና የጤና ባለሙያዎች ጋር በመሆን ጤናን ፣ ደህንነት እና በጤና እንክብካቤ ሥርዓቱ ላይ ያለን እምነት ለማሻሻል በጋራ እንሰራለን።

- አገልግሎቱ ነጻና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው።
- በሴቶች ሆስፒታል የአፍሪካ ሴቶች ክሊኒክን መገልገል ለሚፈልጉ ሴቶች ድጋፍ እናደርጋለን።



## ያግኙን

**ሮያል የሴቶች ሆስፒታል (ሮያል ዊመንዝ ሆስፒታል)**
20 Flemington Road, Parkville VIC 3052
(03) 8345 2000

**የቤተሰብና የስነ ተዋልዶ መብቶች ትምህርት መርሃ ግብር (FARREP)**
(03) 8345 3058
Farrep.Program@thewomens.org.au

**የአፍሪካ ሴቶች ክሊኒክ**
(03) 8345 3058
africanwomensclinic@thewomens.org.au

**ስለ FARREP እና ስለ አፍሪካ ሴቶች ክሊኒክ የበለጠ ይወቁ፡-**



**የአስተርጓሚ አገልግሎት**
(03) 8345 3054

AMHARIC

# FARREP



# የቤተሰብ እና የስነ ተዋልዶ መብቶች የትምህርት መርሃ ግብር

በሴት ልጅ ግርዛት (FGC) የተጎዱ ሴቶችን እና ማህበረሰብን ማገዝ



ነጻ፣ ሚስጥረኝነቱ የተጠበቀ እና በመላው ስቴት (ግዛት) የሚገኝ

the women's
the royal women's hospital

## አገልግሎቶቻችን

- በሴቶች ሆስፒታል የክሊኒክ ቀጠሮዎች ወቅት ድጋፍ መስጠት
- ለልዩ (ስፔሻላይዝድ) ህክምና የአፍሪካ የሴቶች ክሊኒክን መጠቀም
- ስለ ሴት ልጅ ግርዛት (FGC) እና የስነ ተዋልዶ ጤና የጤና ትምህርት እና ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ለጤና አገልግሎቶች ለባህል ተስማሚ የሆነ ድጋፍ መስጠት
- ለጤና ባለሙያዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት (FGC) እና የባህል ግንዛቤ ስልጠና መስጠት

**የFARREP ቡድናችን አባላት፣ ልምድ ያላቸው የሴት የባህል ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ናቸው።**



## የFARREP አገልግሎትን ማግኘት የሚችለው ማን ነው?

- **የሴት ልጅ ግርዛት (FGC) ያጋጠማቸው ሴቶች**
- **የሴት ልጅ ግርዛት እንዳጋጠማቸው ማወቅ የሚፈልጉ ሴቶች**
- **ምክር ወይም ድጋፍ የሚፈልጉ የጤና ባለሙያዎች**



## እንዴት መጠቀም እንደሚቻል



**ሰዎችን ለመጠቆም FARREPን ያግኙ፡**

(03) 8345 3058
Farrep.Program@thewomens.org.au

## ጥብቅና እና ማብቃት

የሴት ልጅ ግርዛትን (FGC) ለመከላከል ጥብቅና እንቆማለን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ አዎንታዊ ለውጥን እናበረታታለን፣ እንዲሁም ሴቶችን እና ቤተሰቦችን እናበቃለን።

ስራችን በአውስትራሊያ የጤና ሥርዓት ውስጥ ግንዛቤን እና እምነትን ይገነባል፣ እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን እና የማህበረሰብ አጋሮችን ክህሎት ያጠናክራል።





## ስልጠና እና ትምህርት

**ለጤና ባለሙያዎች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ነጻ ስልጠና እንሰጣለን።**

ስልጠናዎቻችን በዋናነት የሚያተኩሩት በሴት ልጅ ግርዛት (FGC) የተጎዱ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ በሚያስችል ስነ-ልቦናዊ ጉዳትን (trauma) ባገናዘበ እንክብካቤ እና የባህል ግንዛቤ ላይ ነው።

**ቀጠሮ ለማስያዝ FARREPን ያግኙ፡-**

(03) 8345 3058
Farrep.Program@thewomens.org.au